የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
Ministry of Labor and Skills

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴ/ሙ/ስ/ ዘርፍ

## በ2018 ዓ.ም ስልጠና ዘመን
## የመደበኛ ስልጠና መርሀ ግብር የመግቢያ ነጥብ

ጥቅምት 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አገራችን ለነደፈችው ቀጣይነት ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት የማህበረሰቡን ኑሮ በዘላቂነት ለማሻሻል ድህነትን ማስወገድ የሚችሉ ብቁ፣ ስራ ፈጣሪ እና ችግር ፈቺ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።

አገራችን የተለመችውን ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ቀጣይ እና አስተማማኝ እንድሆን እና የብልጽግና ጉዞ በማሳካት ድህነትን በዘላቂነት ለማስወገድ ሰፋፊ አገራዊ የሪፎርም ስራዎች በመስራት ላይ ስትሆን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፋም የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የመንግስት እና የግል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን በተጀመረው የዓለም አቀፍ የጥራት ስራ አመራር ስታንዳርድ መሰረት ደረጃውን በጠበቀ ስልጠና ዜጎችን በተለያዩ ደረጃዎች በማሰልጠንና ብቃታቸውንም በሙያ ብቃት ምዘና በማረጋገጥ ለስራ ገበያው በማቅረብ ድርሻቸውን እንዲወጡ በማድረግ ላይ ነው።

በአገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት አገልግሎት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በማዕከላዊ ደረጃ የተደራጀ ፈተና እንዲወስዱ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ወደ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ወይም ቀጥታ ወደ ሥራው ዓለም እንደሚቀላቀሉ ይጠበቃል። ስለሆነም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ተፈትነው በመደበኛው ፕሮግራም የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን መርጠው ለመግባት የሚፈልጉት ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ውጤታቸውን መሰረት ያደረገ የመግቢያ ነጥብ መወሰን ያስፈልጋል።

በመሆኑም የ2018 የስልጠና ዘመን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሰልጣኞች ቅበላ ላይ የተጠቀሱ ሀሳቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና የስራ ገበያውን የሰው ሀይል ፍላጎት መሠረት በማድረግ የዘመኑን የሰልጣኞች የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የመግቢያ ነጥብ በመወሰን ለክልሎች እና ከተማ መስተዳደሮች ማውረድ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የመደበኛ ሰልጣኞች የቴ/ሙ/ስ መግቢያ ነጥብ ተዘጋጅቷል።

## 2. በ2018 ስልጠና ዘመን የመደበኛ ሰልጣኞች የመግቢያ ነጥብ ለመወሰን የተለዩ ታሳቢዎች፦

- በ2018 የስልጠና ዘመን መቁረጫ ነጥብ መሰረት የሰልጣኞች ድልድል የሚያሳየው 5፡17፡1 ሲሆን ይህም ከኢንዱስትሪው የሰው ኃይል አሰላለፍ እና በ 2017 የስልጠና ዘመን የተከናወኑ የሰልጣኝ ቅበላ አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች ይህንን መሰረት በማድረግ ቅበላውን ሊተገብሩት ይገባል፤
- በመቁረጫ ነጥቡ መሰረት ከፍተኛ ደረጃዎች ላይ ለመሰልጠን የሚያሟሉ ሰልጣኞች በመረጡት ሙያ ለመሰልጠን ዕድል ካላገኙ በገበያው ፍላጎት መሰረት መፈጸም ይገባል ፤
- በደረጃ 5 የመሰልጠን እድል ያለው ሰልጣኝ ለፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ተደራሽ ካልሆነ በቅርበት በሚገኘው ኮሌጅ መሰልጠን እስከሚችልበት ደረጃ በመሰልጠን ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል፤
- ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን መርጠው የሚመጡ ከሆነ አጠቃላይ የሰልጣኞች ቅበላው ቁጥር በታሳቢነት ከተቀመጠው በላይ ሊሆን እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።
- ካለፉት ሶስት ተከታታይ የስልጠና ዘመናት ልምዶች በመነሳት በመደበኛው የስልጠና ፕሮግራም ይሰለጥናሉ ተብሎ ከሚጠበቁት ሰልጣኞች መካከል 30 **በመቶ** የሚሆኑት በአጫጭር ስልጠና ይበቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በ 2018 ዓ.ም. የስልጠና ዘመን ወደ ቴ/ሙ/ስ/ተቋማት ሊገቡ የሚችሉ ሰልጣኞች ብዛት 454,106 ሲሆን ከላይ የተቀመጠው 30% ታሳቢ ተቀናሽ በማድረግ 317,874 ይሆናል።
- በዚህ አመት የተዘጋጀው መቁረጫ ነጥብ የ 2017 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የተፈተኑ ተማሪዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተሰላ በመሆኑ የሚያገለግለውም ለ 2018 የስልጠና ዘመን ብቻ ነው፤
- ሆኖም ግን ከ 2017 የስልጠና ዘመን በፊት የ 12 ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ወደ ዘርፉ መቀላቀል ቢፈልጉ በየዘመኑ በነበረው የመቁረጫ ነጥብ መስፈርት መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል።
- የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ አምጥተው ወደ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሌጆች ገብተው መሰልጠን የሚፈልጉ ተማሪዎች በከፍተኛው የስልጠና ደረጃ በመረጡት ሙያ ተመዝግበው መሰልጠን የሚችሉ ይሆናል።

ሞው የሙያ ደረጃ ስልጥነው ወደ ስራው ዓለም ከተቀላቀሉ በኋላ በድጋሚ ደረጃቸውን ማሻሻል የሚጠይቁ ዜጎችን በቀድሞው እና በአዲሱ የሙያ ደረጃ መካከል ያሉ ልዩነቶችን ስልጠና በመሙላት በተቀመጠው የመግቢያ ነጥብ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል

### ሰንጠረዥ-1 የ2018 ዓ.ም የቴ/ሙ/ስ/መቁረጫ ነጥብ መነሻ ስብጥር

| የክፍል ደረጃ | የኢንደስትሪው የሰው ኃይል አሰላለፍ ስብጥር | | |
|---|---|---|---|
| | ደረጃ-5 (5) | ደረጃ 3 እና 4 (17) | ደረጃ 1እና2 (1) |
| 12ኛ ክፍል | 98,718 | 335,644 | 19,744 |
| ጠቅላላ ድምር (454,106)-(30% ወደ አጫጭር ይገባሉ የሚል ታሳቢ) = 317,874 | | | |

## ሰንጠረዥ 2 ለተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ የመግቢያ ውጤት

| ለተፈጥሮና ለማህበራዊ ሳይንስ የመግቢያ ውጤት | | | |
|---|---|---|---|
| የስልጠና ደረጃዎች | የወሰዱት ፈተና | የተማሪዎች ዓይነት | መቁረጫ ነጥብ |
| ደረጃ 1 እና 2 | የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 134 እና ከዚያ በታች |
| | | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 132 እና ከዚያ በታች |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 121 እና ከዚያ በታች |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 120 እና ከዚያ በታች |
| | | ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች | 120 እና ከዚያ በታች |
| ደረጃ 3 እና 4 | የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 135 እና ከዚያ በላይ |
| | | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 133 እና ከዚያ በላይ |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 122 እና ከዚያ በላይ |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 121 እና ከዚያ በላይ |
| | | ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች | 121 እና ከዚያ በላይ |
| ደረጃ 5 | የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 179 እና ከዚያ በላይ |
| | | ወንዶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 168 እና ከዚያ በላይ |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢን ሳይጨምር | 168 እና ከዚያ በላይ |
| | | ሴቶች አርብቶ አደር አካባቢዎች | 157 እና ከዚያ በላይ |
| | | ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች | 142 እና ከዚያ በላይ |